# የወሃቢ.ን አሸባሪነት ካጋለጠው የአውሮፓ ሪፖርት ባሻገር

ሸረፋ ከድር

ksherefa@yahoo.com

ከመሰንበቻው የአውሮፓ ህብረት ፓርላማ የኢፌዴሪ መንግስት “በሃይማኖት ሽፋን የተሰለፉ የወሃቢ/ሰለፊ አሸባሪዎች በውጭ ኃይሎች ምንዳ የሰላማዊውን ሙስሊም የአምልኮ ነፃነት እያወኩት ነው” በማለት ደጋግሞ የሚገልፀውን ዕውነታ ይበልጥ ያረጋገጠ ሪፖርት አውጥቷል። አዎ! ሪፖርቱ መንግስት የሀገራችንን ወሃቢ ቡድን የሚመሩት ጥቂት በፔትሮ ዶላር የሰከሩ ምንደኞች፣ ፖለቲከኞች እንጂ ሃይማኖተኞች አለመሆናቸውን በየጊዜው የገለፃቸውን ሃቆች በማያሻማ ሁኔታ ያስረዳ ነው— በእነዚህ “ፖለቲካዊ ሲራራ ነጋዴዎች” ላይ በየጊዜው እየወሰዳቸው የመጣው የእርምት ርምጃዎች ተገቢና ትክክለኛ እንደሆኑም የሚያመላክት ጭምር።

በህብረቱ ፓርላማ የውጭ ፖሊሲዎች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል የቀረበው ይህ ሪፖርት፣ በነዳጅ ሃብቷ በምትታወቀው ሳዑዲ ዓረቢያና በአጎራባቾቿ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚያሸብሩትን የወሃቢ.ንና የሰለፊን ቡድን ሚሊሻዎች በመደገፍ ተግባር ፋታ እንዳጡ ያስረዳል። በዚህም ቡድኖቹ በዓለም ላይ ላሉ አማፂዎች እንዴት አድርገው የመሳሪያ አቅርቦትና ድጋፍ እንደሚያደርጉም አስረድቷል።

ከዚህ በተጨማሪም የወሃቢ/ሰለፊ ድርጅቶችን አደገኛነት አስመልክቶ “ማንኛውም የሙስሊሙ ዓለም ሀገር ከቡድኖቹ ዘመቻዎች ነፃ አይደለም።...የእነርሱ የሁልጊዜ ዓላማ ተቃዋሚዎቻቸውን ማሸበርና በደጋፊዎቻቸው ውስጥ አድናቆትን መፍጠር ስለሆነ ነው” በማለት የማስጠንቀቂያ አስተያየቱን አስፍሯል። እንደ ፓርላማው ሪፖርት ከሆነ፣ የነዳጅ ባለፀጋዋ ሳዑዲ ዓረቢያና ትንሿ፣ነገር ግን አብታሟ ኳታር ቡድኖቹን በአረብ ምግባረ-ሰናይ ድርጅቶች አማካኝነት ቡድኖቹን ይደግፋሉ።

እናም ወሃቢዝምን ለመደገፍ ሲባል እስካሁን ድረስ ሳዑዲ ብቻ 10 ቢሊዮን የሚሆን ዶላር እንዳወጣች የሚገመት ሲሆን፣ አዲሷ የጉዳዩ ተቀላቃይ ኳታር ደግሞ ከሊቢያ እስከ ሶሪያ የሚገኙ የሚሊሻ ቡድኖችን ረድታለች። በዚህም ሳቢያ የወሃቢ.ን/ሰለፊን አስተምህሮት በሚደግፉ የዓረብ ምግባረ-ሰናይ ድርጅቶችና በፅንፈኛ እስላማዊ አራማጆች መካከል የተፈጠረው ቁርኝት ለዓለም ህዝቦችና መንግስታት ዋነኛ ስጋት መሆኑን ሪፖርቱ አትቷል። እርግጥም ሪፖርቱ በይፋ ወሃቢ.ና ሰለፊ የዓለም አቀፍ አሸባሪዎች መፈልፈያ ማዕከል እንደሆኑ ማተቱ፣ ቡድኖቹ ምን ያህል የዘመነ ሉላዊው (Globalization) ሰላማዊ ምህዳር ጋሬጣ መሆናቸውን በገሃድ የሚያሳይ ነው።

እርግጥም እንዲህ ዓይነቱን ተጨባጭ ሪፖርት የተመለከተ ማንኛውም ሰው እንደ ዜጋ ብዕሩን ከወረቀት ጋር ማገናኘቱ የሚቀር አይመስለኝም–ሀገራችን ውስጥ የተፈጠረውን የሽብተኝነት አደጋ ከዚህ በላይ ግልፅ በሆነ እማኝነት ማረጋገጥ አይችልምና። እናም ከወሃቢያ/ሰለፊ ጥቂት ቡድኖች አሸባሪነት ባሻገር፣ ሀገራችን ውስጥ ያለውን ነባራዊ ሃቅ ለውድ አንባቢዎቼ ለማሳየት የበኩሌን ለማለት ፈቀድሁ።…

አዎ! በዓለማችን ላይ የሰላም ሰንኮፍ ሆኖ በአውሮፓ ህብረት ፓርላማ ሪፖርት የተገለፀው የወሃቢዝም እንቅስቃሴ የአሸባሪነት ተግባር እንጂ ከሃይማኖት ጋር አንዳችም ትስስር እንደሌለው ተረጋግጧል። ዓላማውም የጥቂቶች እምነትን ለማስፋፋት ሲባል የብዙሃኑን ምዕመን የእምነት ነፃነት በመደፍጠጥ የራስን ዕምነት በሌሎች ላይ በሃይል ጭኖ እስላማዊ መንግሰት የመመስረት ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ተግባርን መከወን እንደሆነም ጭምር። ታዲያ ሀገራችንም ከዓለም ተነጥላ እንደ ደሴት ለብቻዋ መኖር ስለማትችል፣ ምናልባትም ይኸው ኢ-ዴሞክራሲያዊ ሴራ ሊያንዣብብባት ቢችል የሚገርም አይሆንም– ምንም እንኳን በአዲሲቷ ኢትዮጵያ ውስጥ ለእንዲህ ዓይነቱ የዜጎችን መብት በሽብር ተግባር ለሚደፈጥጥ ነውረኛ እሳቤ ተስማሚ የሆነ አውድ ባይኖርም።

ታዲያ እዚህ ላይ ‘የሪፖርቱ የአሸባሪነት እውነታ ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አኳያ ሲታይ ያለው አንድምታ ምን ይመስላል?’ ብሎ መጠየቅ አስፈላጊ ይመስለኛል። ምክንያቱም የጉዳዩን ሃቅነት ስንመረምር ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የወሃቢን የግብረ-ሽበራ ፍላጎት ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ ፍንትው አድርጎ ስለሚያሳየን ነው። ማንኛውም የዚህ ፅሑፍ አንባቢ እንደሚያውቀው በአክራሪነትና በአሸባሪነት ሳቢያ ከሚፈፀሙ አደጋዎች ውስጥ በህዝብ ህይወትና ንብረት ላይ የሚፈጸሙ ጅምላ ጭፍጨፋዎች በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ተግባራቱ በባህሪያቸው ንፁሃን ህዝብን ዒላማ የሚያደርጉ  በመሆናቸው፤ ዳፋው የሚተርፈው ከድህነት አዙሪት ቀለበት ወጥቶ ራሱንና ሀገሩን ለመለወጥ ደፋ ቀና በሚለው ሰላማዊ ዜጋ ላይ ነው፡፡

ሀገራችን ውስጥ ከተከናወኑ የሽብር ተግባራት መካከል በርካታ አብነቶችን መጥቀስ ቢቻልም ቅሉ፤ የአንድ ወቅት ሁኔታን ብንመለከት እንኳን በኦነግ ወይም ኦነግ በነበሩ ሰዎች አማካኝነት “ካዋርጅያ” የተባለ የሙስሊም አክራሪዎች የተቀመረ የጥፋት እንቅስቃሴን ማውሳት ይቻላል፡፡ በወቅቱ እነዚህ ወገኖች በብሔር መብት ዙሪያ ያካሄዱት እንቅስቃሴ ሃቁን በሚገነዘበው ህዝብ ተቀባይነት በማጣቱ፤ የሸፍጥ ማርሻቸውን ወደ ሃይማኖት በመቀየር በምዕራቡ የሀገራችን ክፍል በርካታ ዜጎች ለህልፈተ-ህይወት እንዲዳርጉ እንዲሁም ቤት ንብረታቸው እንዲወድም አድርገዋል፡፡ ምንም እንኳን እነዚህ ሃይሎች ይዘውት የተነሱት ዓላማ በህዝቡ ርብርብ የከሸፈ ቢሆንም፤ ይህን መሰሉ በሃይማት ሽፉን የሚደረግ የአሸባሪነት ተግባር በዋነኛነት የሚጎዳው ህብረተሰቡን መሆኑን አመላክቶ አልፏል፡፡

የሽብርተኛነትን አደጋ ከሀገራችን አኳያ በሌላኛው የጥፋት ዘውጉ ስንመለከተው ደግሞ፤ የተጀመሩና በማበብ ላይ የሚገኙ የልማት ትልሞችን የሚያቀጭጭ መሆኑን ለመረዳት አይከብድም። እናም አሸባሪዎቹ የሚያልሙት እስላማዊ መንግስትን የመመስረት ህልም የሀገሪቱን ሰላም ማወክ መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው፡፡

ሁላችንም እንደምንገነዘበው ሰላም ከሌለ ስለ ልማትና ዴሞክራሲ ማሰብ የዋህነት ነው። ምንም እንኳን በአሁኑ ወቅት የተፋጠነ ልማትን ለማምጣት የኢፌዴሪ መንግስት ትክክለኛ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ይዞ ውጤት በማምጣት በዓለም ላይ ተምሳሌታዊ የልማት ፋና መሆን ቢችልም፤ ዘላቂና አስተማማኝ ሰላም ከሌለ ግን እንቅፋት መፈጠሩ የሚቀር አይመስለኝም፡ ፡ ይህ ደግሞ በሀገራዊ ህልውናችን ላይ የራሱን አሉታዊ አሻራ ማሳረፉ አይቀሬ ነው። ከዚህ አኳያ የአውሮፓ ፓርላማ ሪፖርት ብሔራዊ ደህንነታችንን ከማስጠበቅና የኋሊት እንዳንመለስ በማድረግ ረገድ ዕውነታውን እኛም ሆንን ሌሎች ይበልጥ እንድናውቀው አድርጎናል ነው ማለት ይቻላል።

ታዲያ እዚህ ላይ አንድ ዕውነታን ልንክድ አይገባም። እርሱም የማንኛውም ሀገር መንግስት ብሔራዊ ደህንነቱን የማስጠበቅ ኃላፊነትና ግዴታ ያለበት መሆኑን ነው። ለምሳሌ ያህል አሜሪካንና የምዕራቡ ሀገራትን ብንመለከት እንኳን በእነ አል-ቃዒዳ የተደቀነባቸውን የሽብርተኝነት እንቅስቃሴ ለመግታት ሀገር ውስጥ ከሚያከናውኑት አደጋውን የመከላከል ተግባር ባሻገር፤ ችግሩን ከመሰረቱ ለመቅረፍ ባህር ተሻግረው አፍጋኒስታን ድረስ በመዝለቅ ሰራዊቶቻቸው እዚያው ለበርካታ ዓመታት መከተማቸውን አንዘነጋውም። ይህም የአንድ ሀገር መንግስት ብሔራዊ ደህንነቱን ለማስጠበቅ ምን ያህል ርቀት ሊጓዝ እንደሚችል የሚያመላክት ነው። እናም "ድህነት ዋነኛ ጠላታችን ነው" በማለት ተመፅዋችነትትን ኮንኖ መላው ህዝቡን በፈጣኑ የዕድገት ባቡር ላይ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ማሳፈር የቻለው የኢትዮጵያ መንግስትም፤ ከዚህ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ካለው ነባራዊ ሁኔታ ውጪ ሊሆን አይችልም– የሀገሩን ብሔራዊ ደህንነት ማስጠበቅ ግዴታው ስለሆነ።

በመሆኑም ሌሎች ሀገሮች አሸባሪነትን ለመዋጋት ባህር አቋርጠው እየዘመቱ ባሉበት ሁኔታ፤ የሀገራችን መንግስት ግን እዚሁ ሀገሩ ውስጥ በ"ወሃቢያ" የተደቀነብንን የሽብር አደጋ መመከቱ፣ ህጋዊ ርምጃዎች መውሰዱና ህዝቡም ሃቁን እንዲያውቀው አድርጓል። ይሁንና የትግል ስልታቸው አንድ ዓይነት የሆኑት የሀገራችን የእውር ድንብር ተቃዋሚዎች የጉዳዩን ስረ-ነገር ሳይረዱ መንግስት 'ህገ-መንግስቱን እየጣሰ ነው' በማለት ተራ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት መሞከራቸው አሳፋሪ ነው።

እርግጥ የአክራሪዎቹ ጉዳይ ከህገ-መንግስት መጣስ ጋር እንደምን ሊገናኝ እንደሚችል የሚያውቁት የሃሳቡ አራማጆች ብቻ ናቸው። ያም ሆነ ይህ ግን የሽብርተኝነት አጀንዳ በዋነኛነት

የሀገራችንን ሁለንተናዊ ዕድገት የሚገድብ ብቻ ሳይሆን፤ ከነበርንበት የልማት ማማ ላይ የኋሊት እንድንሽራተት ብሎም እርስ በርስ እንድንጋጭ የሚያደርግ በመሆኑ፤ ህዝቡ መንግስት ይህን አደገኛ ተግባር “ሳይቃጠል በቅጠል” ማለቱ እጅግ ተገቢና የሚያስመሰግነው ነው። ለምን ቢባል፤ የአውሮፓው ፓርላማ ሪፖርት በማያሻማ ሁኔታ ያረጋገጠው ጉዳይ በየትኛውም ሀገር የሚገኙ “የወሃቢዝም” አራማጆች አሸባሪዎች መሆናቸውን ነው። እናስ ነገርን ሳያጣሩ ለመቃወም ብቻ የሚቃወሙት ለአቅመ-ተቃዋሚነት ያልደረሱት የሀገራችን ተቃዋሚ ተብዬዎች አሁንስ ምን ይሉ ይሆን?...ማን ነበር “የቅሌት ቀን አይመሽም” ያለው?...

ለሀገራችን የደፈና ተቃዋሚዎች የአሸባሪነት ምንነትና ዓላማ ምን እንደሆኑ የሚያውቁት እነርሱ ቢሆኑም፤ መንግስት ግን በሀገሩ ውስጥ በሃይማኖት ሰበብ በሚፈጠር ግጭት የሚታመስ ህብረተሰብ ስለ ልማት ሊያስብ እንደማይችል ይገነዘባል፡፡ ምክንያቱም የዜጎች ካፒታልና ጉልበት በሰላማዊ ሁኔታ ካልተንቀሳቀሱ የሀገርን ዕድገት ሊያረጋግጡ ስለማይችሉ ነው፡፡ ከውጭ ኢቨስት ለማድረግ የሚመጣው ባለሀብትም ቢሆን አስተማማኝ ሰላም ከሌለ ማፈግፈጉ የማይቀር መሆኑም እንዲሁ፡፡ እርግጥም ሁኔታው በድምሩ ሲታይ በሃይማኖት ሰበብ የሚከናወኑ ማናቸውም ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ተግባራት የሀገራችንን የመልማት ብሎም የህዝቦቿን የተጠቃሚነት ዕድል በአያሌው የሚገደብ ነው፡፡ እናም የአሸባሪዎቹ የጥፋት እንቅስቃሴ መታየት ያለበት ከዚህ ሀገራዊ ዕውነታ አኳያ መሆን ያለበት ይመስለኛል፡፡

ይህ ብቻ አይደለም። በአውሮፓ ህብረት ማንነታቸው ተብጠርጥሮ የተገለፀው የወሃቢ/ሰለፊ አሸባሪዎችን እኩይ ፍላጎት በሀገራችን ውስጥ ስር በመስደድ ላይ ከሚገኙት የሰብዓዊና የዲሞክራሲያዊ መብቶች እመርታ እንቅፋትነት አኳያም ልንመለከተው እንችላለን፡፡ አዎ! በተለያዩ ጊዜያት ሀገራችን ውስጥ የሽብር ተግባር ለመፈፀም ሲያስቡ እጅ ከፍንጅ የተያዙ ግለሰቦች የእምነት ቃል እንዳዳመጥነው፤ ቢሳካላቸው ኖሮ ሃሳባቸው ሰዎችን አሰልጥኖ በኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ላይ የ“ጀሃድ” ጦርነት ማወጅ ነው— ከፍ ሲልም ቀደም ሲል የጠቀስኩትን እስላማዊ መንግስት መመስረት። ታዲያ ይህ አስተሳሰብ የራስን እምነት በሌሎች ላይ በሃይል የመጫን ኢ-ሰብዓዊና ፀረ-ዲሞክራሲያዊ እሳቤን የሚያሳይ ነው፡፡ እነዚህ የፍርድ ብይን የተሰጣቸውና ተጠርጣሪ አሸባሪዎች በሚያስቡት መልኩ ሁኔታዎች ቢሟሉላቸው ኖሮ፤ ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ፤ የመከራከርና ምክንያታዊ በሆነ መንገድ የመሸናነፍ ዕድል ከነ አካቴው መጥፋቱ አይቀሬ ነው፡፡ እናም የሀገራችን ህዝቦች መብታቸውን ጉልበተኞች በሚሰጧቸውና በሚነፍጓቸው ልኬት መጠን መጠቀም ይጀምራሉ፡፡

ታዲያ አሸባሪዎቹ መብት ሰጪና ነሺ ሆነው መልካም አስተዳደርን መደፍጠጣቸው አይቀርም፡፡ እምነታቸው “ጅሃድ” በሚል የሃይል አመለካከት የህዝብን ስልጣን በጉልበት መያዝ

በመሆኑም፤ በሚቆሰቁሱት የእሳት ቋያ ለህልፈተ-ህይወት የሚዳረገው ወገን፣ የሚጠፋው ንብረት ከፍተኛ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ ታዲያ በእንዲህ ዓይነት የለየለት ፀረ-ህዝብ ተግባር የሚገኝ ስልጣን፤ መልሶ ህዝቡን እንደ እግር እሳት የሚለበልብ መሆኑን ሩቅ ሄደን ሌሎች ተመሳሳይ አስከፊ ተግባራት ሳንጠቅስ፤ ቅርባችን ካለችው ጎረቤታችን ሶማሊያ መማር የምንችል ይመስለኛል፡፡

በመገናኛ ብዙሃን በተለያዩ ጊዜያት እንደተመለከትነው፤ ወንድም የሆነው የዚያች ሀገር ህዝብ፤ በአል-ሸባብ ኢ-ሰብዓዊና ፀረ-ዲሞራሲያዊ አገዛዝ ስር በነበረበት ወቅትና ነፃ ከወጣ በኋላ ልዩነቱን የገለፀው ቀዳሚ ጊዜውን “አልኖርኩም” በሚል ነው፡፡ እርግጥም በገዛ ህዝቡ ላይ “ጅሃድ” አውጆ በተለያዩ የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ ስልጣን ይዞ የነበረው የሽብር ቡድኑ (የዛሬን አያድርገውና)፤ በተቆጣጠራቸው አካባቢዎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ጨፍልቋል። ለምን ፊልም ተመለከትክ?፣ ሙዚቃ ያለበት ቴሌቪዥን አየህ? …ወዘተ. በማለት ህዝቡን ቁም ስቅሉን አሳይቶታል፡፡ በድንጋይ ወግሮታል፤ በጅራፍ ገርፎታል፤ በ“ሹራ” ምክር ቤቱ አማኝነትም ፍርድ እያሰጠ አስገድሎታል። ለዚህም ነው— በአሁኑ ወቅት በሶማሊያ ፌዴራላዊ መንግስት ስር ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ በመተዳደር ላይ የሚገኘው የዚያች ሀገር ህዝብ የአል-ሸባብን አገዛዝ የገሃነም-እሳት ያህል በመቁጠር በይፋ በማውገዝ በምሬት ተንገሽግሾ ሲናገር የምናደምጠው፡፡

አዎ! በሀገራችን ውስጥ ያሉት የወሃቢ/ሰለፊ የፔትሮ ዶላር አቀንቃኞች ቢሳካላቸው ልክ እንደ አል-ሸባብ ሁሉ ሊያመጡት የሚፈልጉት የፖለቲካ አስተሳሰብ ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ ምክንያቱም እነዚሁ አሸባሪዎች በተለያዩ ወቅቶች እንደተናገሩት፤ አክራሪዎችን በመመልመል ከሚሴን እንደ አፍጋኒስታን በመቁጠር “ጅሃድ” ለማካሄድ ሲያልሙና የሚያበጣብጡ ፅሑፎችን ሲያዘጋጁ የነበሩ በመሆናቸው ነው፡፡ እርግጥም እነዚህ ሃይሎች ከዚህ የመንደርደሪያ ሃሳባቸው በኋላ የእነ አል-ሸባብን፣ የእነ ቦኮ ሃራምንና የእነ አንሳር ዲንን ሞዴል እንደሚከተሉ ከማንም ሊሰወር አይችልም። ተግባሩ በአውሮፓው ሪፖርት ላይ እንደተገለፀው ዓለም አቀፍ ትስስር ያለው ነውና። ከትስስሩ አኳያ የአንድ ሰሞን አስረጅን ማንሳት ይቻላል።

በሙስሊሙ ስም ተንቀሳቅሰው ሰሞኑን “ጅሃዳዊ ሃራካት” በሚል ስያሜ በመገናኛ ብዙሃን ያየናቸውና ዓላማቸው እስላማዊ መንግስት መመስረት መሆኑን በራሳቸው አንደበት ያደመጥናቸው ተጠርጣሪ አሸባሪዎች ውጫዊ የትስስር ድራቸው ለዚህ አባባሌ ሁነኛ አስረጅ ነው። የግብፁ የሙስሊም ወንድማማቾች ፓርቲ ርዕዩተ-ዓለም አቀንቃኝ የሆኑት የሼክ ሻኪር አልሳይድ ከዋሽንግተን ዲሲ ያሰሙት አስገራሚ መፈክር ተጠቃሽ ነው። በወቅቱ ዲሲ ውስጥ በፅንፈኛ ዲያስፖራዎች አዘጋጅነት በተዶለተው መድረክ ላይ የተሰማው የሼኩ መፈክር “የኃይል ምንጫችን መሳሪያ ነው። በዓለም ላይ ያሉ ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ሁሉ በኢትዮጵያ መንግስት ላይ

እንዲነሱ ማነሳሳት አለባችሁ። አሁን ያለው መንግስት የክርስቲያኖች መንግስት ስለሆነ ሁላችሁም ይህን መንግስት ለመጣል መነሳሳት ይኖርባችኋል" የሚል ቀጭን ትዕዛዝ ነው። ታዲያ ይህን አባባል በአጭር ቋንቋ "በዓለም ላይ የምትገኙ ኢትዮጵያዊያን ነውጠኞች ተባበሩ" የማለት ያህል ነው ብሎ ብቻ መተርጎም አይቻልም፤ "እኛም በውስጥ ጉዳያችሁ ጣልቃ ገብተን እናግዛችኋለን" የሚል ጭምርም እንጂ።

ምንም እንኳን ላለፉት በርካታ ጊዜያት በድብቅ የኢትዮጵያን ፅንፈኞች ሲመክሩና በህቡዕ ሲያሰማሩ የነበሩት እኚህ ግለሰብ ዛሬ ላይ የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ለአክራሪዎች ቦታ የሌለው መሆኑን ሲገነዘቡ፤ ትዕግስታቸው ተሟጦ በግልፅ በተዘጋጀ መድረክ ላይ ያለ እንዳች ሃፍረት በጣልቃ ገብነት መናገራቸው እርግጥም የኢትዮጵያ መንግስት በአሸባሪዎችና በተጠርጣሪ አሸባሪዎችን ላይ የወሰደው እርምጃ ትክክለኛ መሆኑን ከማመላከቱም በላይ በአውሮፓው ህብረት ፓርላማ ላይ የተጠቀሰውን የአሸባሪነት ትስስር ድርን የሚያሳይ ነው። በወሃቢ/ሰለፊ ስም የሌሎችን የእምነት ነፃነት በመፃረር የራስን ፍላጎት በሌሎች ላይ በሃይል ጭኖ ህዝቦችን በፀረ-ዴሞክራሲያዊነት በትር የመግረፍ አባዜም ጭምር።

ግና አሜሪካ ተቀምጦ ኢትዮጵያ ውስጥ "ንፋ መለከት ክተት ሠራዊት" የሚባልበት ምህዳር የሌለ መሆኑን ማወቅ ይኖርባቸዋል። ለምን ቢባል፤ ሀገራችን ውስጥ መንግስትን የመሾምና የመሻር ሉዓላዊ የስልጣን መብት የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች እንጂ፣ በሃይማኖት ስም የሚንቀሳቀሱ ፖለቲከኞችና ተከታዩቻቸው ባለመሆኑ ነው። ከዚህ ውጪ የህዝቦችን መብት በመደፍጠጥ ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱን በኃይል ለመናድ 'እኔ አውቅላችኋለሁ' ማለት ከስልጣን ባለቤቱ ጋር በቀጥታ መላተም መሆኑን ሼኩም ይሁኑ ጀሌዎቻቸው ማወቅ አለባቸው።

እንደሚታወቀው የሀገራችን ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በህዝቡ ፍትሐዊ ድምፅ የተመሰረተ ነው፡፡ የሥርዓቱ ምሶሶ የሆነው ህገ- መንግስታችን ደግሞ በሁሉም የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ፍላጎትና እምነት ጸድቆ ስራ ላይ የዋለ ሰነድ ነው፡፡ ስለሆነም እያንዳንዱ ዜጋ ለዚህ ሰነድ ጥብቅና ይቆማል። እናም ከሰነዱ ጋር መጋጨት በቀጥታ የስልጣኑ ባለቤት ከሆነው ህዝብ ጋር መላተም መሆኑን የመፈክሩ ዲስኩረኛ ሊረዱት ይገባል፡፡ በመሆኑም በአሁኑ ወቅት በሃይማኖት ስም የተደራጁ አሸባሪዎችን የሚያስተናግድ ምህዳር ሀገራችን ውስጥ የሌለ መሆኑን ማወቅ የሚበጅ ነው።

ይሁንና ማንም ያሻውን ቢልም፣ እኛ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ባህል እየተገነባ ባለበት ሀገር ውስጥ የምንኖር ዜጎች እንደ መሆናችን መጠን፤ ይህኛው ወይም ያኛው ሃይማኖት በኃይል እንዲጫንብን መፍቀድ አይኖርብንም፡፡ ሃይማኖት የግል እንጂ የጋራ ባለመሆኑ፤ ምርጫው ለተከታዩ መተው ይኖርበታል። በዴሞክራሲያዊ እሳቤ ውስጥ ለግለሰብ መተው የሚገባው ሃይማኖታዊ ምርጫ መንግስትም ሆነ ሌሎች የውጭ ሃይሎች ጣልቃ እንደማይገቡበት በመገንዘብ፤ የአሸባሪዎቹም ይሁን የትስስር ድሩ መሪዎች ዓላማ በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ውስጥ ቦታ የሌለው መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው፡፡ እርግጥ የአሸባሪዎቹና የትስስሩ ድር መሪዎች ያልተሳካ እንቅስቃሴ ሀገራችን ያለችበትን ተጨባጭ ሁኔታ የማያመላክትና ገፅታችንን ለማጠልሸት የቀረበ መሆኑን በእርግጠኝነት መግለፅ ይቻላል፡፡

ሁላችንም እንደምናውቀው ሀገራችን ተዓምራዊ በሚባል የለውጥ ሂደት ውስጥ ናት፡፡ ይህ ለውጥ ከ85 በመቶ በላይ የሆነውን የሀገራችን አርሶና አርብቶ አደር ህይወትን እየቀየረ መሆኑን እንደ የዓለም ባንክ የመሳሰሉ ታላላቅ ተቋማት እንዲሁም የሌሎች ሀገራት መሪዎች ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል፡፡ ይህም ቀደም ባሉት ስርዓቶች በረሃብና በተመፅዋችነት የምንታወቅበት ገፅታችን ዛሬ በዴሞክራሲያዊውና ልማታዊው መንግስታችን እየተቀየረ መሆኑን የሚያመላክት ነው። ሌላው ቀርቶ መልካም ነገር ፈፅሞ የማይዋጥላቸውና ቃር…ቃር የሚላቸው የሀገር ውስጥ ተቃዋሚዎች እንኳን ሳይቀሩ ሊክዱት በማይችሉበት ደረጃ ሀገራችን በሁሉም መስኮች በመለወጥ ላይ መሆኗን እያመኑ ነው፡፡ ይህ ግን ዓለም አቀፍ ተቀባይነትን በማግኘት ላይ የሚገኘው ስኬታችን እንዳይታይ የሚፈልጉ ሃይሎች የሉም ማለት አይደለም፡፡ በቀዳሚነት የሚጠቀሰው ሁሌም የኢትዮጵያን ስኬቶች ሲያይ ዓይኑ ደም የሚለብሰው የኤርትራ መንግስት ነው።

በአውደ-ውጊያ ግንባር ላይ የሽንፈት ፅዋን የተጎነጨውና በዲፕሎማሲው መስክም ከዓለም የተነጠለው የአምባገነኑ ኢሳያስ አፈወርቂ መንግስት የትርምስ ስትራቴጂውን በማጠናከር በሀገራችን ሃይማኖት ውስጥ የተላላኪነት እጁን ማስገባቱን ራሱ አምኗል። በራሱ አንደበት የተናገረው እምነትም "…ለሰባት ዓመታት ያህል በአል-ሸባብ አማካኝነት ተጠቅመንበታል። አሁን ደግሞ ይህ ችግር በኢትዮጵያ ውስጥ በፈጠርነው አል-ሸባብ አማኝነት በገሃድ እየታየ ነው። በኢትዮጵያ መስጊዶች ውስጥ እየታየ ያለው እስላማዊ እንቅስቃሴ የጥረታችን ውጤት ነው" የሚል ነው። እርግጥም የአስመራው ቡድን አውቆም ይሁን ሳያውቅ የአል-ሸባብ የቅርብ አጋርና ስምሪት ሰጪ ብሎም ሀገራችን ውስጥ በሃይማኖት ሽፋን የሚከናወኑ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎችን እየመራ መሆኑን በራሱ ጊዜ አምኗል። የአስመራው አስተዳደር ከአል-ሸባብ ጋር በማበር ከአንዳንድ የውጭ ሃይሎች የተሰጠውን የቤት ስራ ሊፈፅም ደፋ ቀና ብሏል–የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ህልሙን ስላመከነበት ከስሮ ቀረ እንጂ።

እርግጥ ሀገራችን ውስጥ ያለው ዕውነታ ማንኛውም ሃይማኖት ህገ-መንግስታዊ ዋስትና የተሰጠው በመሆኑ፤ በእስልምናም ይሁን በክርስትና ሃይማኖቶች ውስጥ ተቻችሎ መኖርና መከባበር ብቻ ነው። ነገር ግን በሃይማኖት ሽፋን እንደ ተላላኪዎቹ ኤርትራ መንግስትና አል-ሸባብ ያሉ የራሳቸው የሽብር ዓላማ ያላቸው ሁይሎች ሀገራችን ውስጥ አክራሪዎችን አስርገው ለማስገባት በመሞከር ሁከትን ለመፍጠር ይሻሉ— ምንም እንኳን በአሁኑ ወቅት ይህ ተግባራቸው በመምከን ላይ ቢሆንም። እናም ሻዕቢያ እንደሚደሰኩረው ሳይሆን፣ በዚህ ረገድም ያከናወናቸው እኩይ ሴራዎች በህዝብና በፀጥታ ሃይሎች ትብብር ሊሰምርለት ያልቻለ መሆኑን መገንዘብ በጄ ነው። ነገም ሆነ ከነገ ወዲያም እንዲሁ። ምንም እንኳን የአውሮፓ ህብረት ፓርላማ ሪፖርት የወሃቢ/ሰለፊ የአሸባሪዎች መፈልፈያ መሆናቸውን በጥቅሉ ቢገልፀውም፤ ከሀገራችን አኳያ ከሪፖርቱ ባሻገር ያለው ነባራዊ ሃቅ ሲመነዘር ይህን ይመስላል።

ይሁንና ሪፖርቱ የኢፌዴሪ መንግስት ከሰለፊ/ወሃቢያ እንቅስቃሴ አኳያ በእስካሁኑ ያናወናቸው እንደ ህገ-መንግስቱንና ብሔራዊ ደህንነትን ማስጠበቅ፣ በሃይማኖት ስም የሚነገድ ፖለቲካን መከላከልና ህጋዊ ርምጃዎችን መውሰድ እንዲሁም አስቀድሞ የሽብርተኞችን የትስስር ድርንና ሴራን ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ለህዝብ ማሳወቁ ትክክል መሆኑን አረጋግጧል። ከዚህ በተጨማሪም ጥቂት የወሃቢዝም አስተሳሰብ አቀንቃኞች ከውጭ በሚላክ ገንዘብ እየተመሩ ሀገርን በምንዳ ለመበጥበጥ የተሰማሩ መሆናቸውን ለሁሉም ወገኖች ግልፅ አድርጓል። ወሃቢዝም ለሀገራችን ብቻ ሳይሆን ለዓለም ሰላም ስጋት መሆኑንም እንዲሁ። ከሁሉም በላይ ደግሞ የአንድ ሀገር ህዝብ የአስተሳሰቡን አራማጆች ማንነት አውቆ ከወዲሁ ሰላሙን ማስጠበቅ እንዳለበት ማሳሰቢያ የሰጠ ነው ማለት ይቻላል። ታዲያ እኛም ብንሆን እነዚህን ወገኖች ከመካከላችን በመለየት ሰላማችንን በራሳችን ትግል ማስጠበቅ እንዳለብን ላፍታም ቢሆን መዘንጋት አይኖርብንም። አማን እንሰንብት።